+251 (0) 912944937
+251 (0) 930015455
yehaarts@gmail.com
www.yehaarts.com




ተ/ፕ ተሥፋዬ ገሠሠ

“ለሁሉም ጊዜ ላለዉ”
በታደለ አያሌዉ

## ፩) ትውልድ(ቀንና ቦታ)፣ ቤተሠብ፣ ትምህርት

- **የትዉልድ ቦታ፡** ሀረርጌ፣ ኢትዮጵያ
- **የትዉልድ ቀን፡** መስከረም ፲፯፣ ፲፱፻፳፱ዓ.ም.
- **የእረፍት ቀን፡** ታኅሣሥ ፯፣ ፳፻፲፫ዓ.ም.
- **ትምህርት፡** የቄስ ትምህርት (ሀረርጌ)፣ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (ተፈሪ መኮነን፣ አዲስ አበባ)፣ ከፍተኛ ትምህርት (ኖርዝ ዌስተርን፣ አሜሪካ)

## ፪) ሙያ፣ አስተዋጽዖ፣ ተሰጥዖ

→ **በኃላፊነት፡** በሦስቱም ቴአትር ቤቶች (ሀገር ፍቅር፣ ብሔራዊ፣ ባህል አዳራሽ)

→ **በደራሲነት፡** እቃዉ(ቴአትር)፣ መተከዣ (ልብወለድ መጽሐፍ)፣ የመጨረሻዉ መጀመርታ (ልብ ወለድ መጽሐፍ)፣ መልክአ ኡመር(ቴአትር - ትርጉም)፣ ኡመር ሃያም(ቴአትር - ትርጉም)፣ እና ሌሎችም።

→ **በአዘጋጅነት፡** የእሾህ አክሊል፣ ጠልፎ በኪሴ፣ የደካሞች ወጥመድ፣ ሮሚዮ እና ጁሊዬት፣ ማነዉ ኢትዮጵያዊ፣ ቴአትር ሲዳዳ፣ ሰሎሞን እና ሳባ፣ እቃዉ፣ የሺ፣ ተሐድሶ፣ መልክአ ኡመር፣ ሰኔ እና ሰኞ፣ አባት እና ልጅ፣ መንገደኞች እና ሌሎች።

→ **በተዋናይነት**

- **ቴአትር፡** ሐምሌት (እንደ ሐምሌት)፣ ጴጥሮስ ያቺን ሰዓት (እንደ ግራዚያኒ)፣ የድል አጥቢያ አርበኛ (እንደ ግራዚያኒ)፣ እቃዉ (እንደ ዶክተር)፣ መልክአ ኡመር (እንደ ኡመር ሀያም)፣ አሉላ አባ ነጋ

- **ፊልም፡** ገመና (የቴሊቪዥን ድራማ)፣ ሼፉ፣ አልማዜ፣ ዴዝዴሞና፣ ሀብትሽ በሀብቴ፣ ትዉልድ እና ሌሎቹም።

www.yehaarts.com

→ **በመምህርነት፡** በዋናነት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች፣ ክበባት (ለምሳሌ ተሥፋዬ አበበ ተጓዥ የቴአትር ክበብ)፣ በቴሌቪዥን (ስነ-ስኬት፣ በናሁ ቴሊቪዥን)

## ፫) መሰናክሎች፣ ማለፊያ ጥንካሬዎች

ያን ያህል ባይሆንም፣ የቆዳ ቀለሙ ለወጥ ማለቱ ዐይን ላይ ያስገባዉ ነበር። በዚያም ላይ አያቱ ቆለጭ፣ የተፈሪ መኮነን (በኋላ ዐጼ ኃይለ ሥላሴ) ሞግዚት ስለነበሩ፣ ከመኳንንት ወገን ነዉ። በመሆኑም በኋላ ደርግ በመጣ ጊዜ፣ የመሳፍንት እና የመኳንንት ወገኖችን እያደነ ሲያስር፣ እሱም ለእስር ተዳርጎ ነበር።

## ፬) እሱን አጥተን ያጣነው ነገር

አንድ ቃል ነበረዉ። ሁልጊዜም በያመቱ ቢያንስ አንድ መጽሐፍ አሳትማለሁ የሚል። እንደቃሉም በዛ ያሉ መጽሐፍትን ከእድሜዉ እና ከንባቡ እየቀዳ እየሰጠን ነበር። የተቋረጠበትን ምክንያት በዉል ባናዉቀዉም፣ በቴሌቪዥን ጀምሮት የነበረዉ “ስነ ስኬት” የሚለዉ መርሐ ግብሩ እጅግ ጠቃሚ ነበር።

## ፭) መርሆች፣ የህይወት ፍልስፍናው

“የወፍ ወንዱ፣ የፖለቲከኛ ሆዱ አይታወቀምና ሁሉን በብልሀት ያዙ” የሚል ምክር ከአፋቸዉ አይጠፋም።

## ፮) ምንጮቻችን

ልዩ ልዩ ቃለ ምልልሶች (ETV - አርሂቡ፣ ጨዋታ ከቴዲ ጋር፣ ድሬ ዩቱብ፣ EBS - ሰይፉ ሾዉ)

www.yehaarts.com